“ዘቦ እዝነ ሰሚአ ለይስማእ።” “የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ።” ማር 4፡23

# ቀኖናዋንና ዶግማዋን የማይጠብቁ ስሟን መጠቀም አይችሉም!

## (በሥርዓቷና በትምህርቷ የማይኖሩ ስሟን መጠቀም አይችሉም!)

## (በሲኖዶሷ የማይመሩ ስሟን መጠቀም አይችሉም!)

### ክፍል አንድ

*ከኢትዮጵያ ውጭ፣ በተለይ በአሜሪካ ሀገር በቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ችግር መሠረት ያደረገ፣ መስከረም 1999 ዓ.ም. ዋሽንግተን ዲሲ*

ይህን ጽሁፍ ለመጻፍ የተገደድነው እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኝነታችንና ልጅነታችን ቤተ ክርስቲያናችን በአንዳንድ ከፖለቲካዊና ግላዊ ጥቅማቸው በስተቀር ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ህልውናና ዓላማ ደንታ በማይሰጣቸው ግለሰቦች ስትዋረድ በጥላዋ ስር ያለነው የሁላችን ውርደት ስለሆነ አይቶ ማለፉ አላፊነትን አለመወጣት ስለሆነብን ነው።

በሌላ አገላለጽ ብልሆቹ አባቶቻችን ሲመስሉ “ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ፣ አብረህ ተወቀጥ” እንደሚሉት ያለችን አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች በጥቂት የፖለቲካ ዓላማቸው ማሳኪያ ያደረጓት ግለሰቦችና አድርባይ መሣሪያዎቻቸው ካህናት ህዝባችን ግራ ተጋብቶ ሲሰቃይ ማየቱና የቤተ ክርስቲያናችን ተቀናቃኞች መሳቂያና መሳለቂያ ሆናና ሆነን እያዩ ዝም ብሎ ማለፍ ራሱ አድርባይነት ሆኖ ስለታየን ነው።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ ወአንትሙሰ ረሰይክምዎ በአተ ፈያት ወሰረቅት”፤ “ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል እናንተ ግን የሌባ፣ የቀማኛ ዋሻ አደረጋችሁት” (ማቴ 21፡12-13) ብሎ በጸሎት ቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሻጮች፣ ቀማኞች፣ ሸፍቶችና ሌቦች እየገረፈ እንዳስወጣቸው በዘመናችንም ከላይ የጠቀስናቸው ግለሰቦች የፖለቲካዊና ግላዊ ዓላማቸው ማሳኪያ ምሽግ ስለአደረጓት የክርስቶስ ተከታዮች የሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁላችን ቤትነስ ቤተ ጸሎት ትሰመይ ወአንትሙሰ ረሰይክምዋ በአተ ፈያት ወሰረቅት ወይም ቤተ ክርስቲያናችን የጸሎት፣ የፍቅር፣ የይቅርታና የአንድነት ቤት ትባላለች እናንተ ግን የፖለቲካ ንዴታችሁንና ብስጭታችሁን መወጣጫ፣ የጥላቻ፣ የስድብ፣ የዛቻ፣  የልመና፣ የዘረፋ፣ የንትርክ፣ የፉከራ ወዘተ... ቤት አደረጋችኋት ብለን የማስወጣት ሀላፊነት አለብን እንላለን።

ውድ አንባቢዎች ወይም አድማጮች፣ የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው የሰላም፣ የፍቅርና የይቅርታ አባት የሆነው ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት፣ አባቶቻችን ለ2000 ዓመታት ያህል በአንድነትና በፍቅር የኖሩባት፣  እስከ ህይወታቸው መጨረሻ ድረስም ህጓንና ሥርዓቷን ትምህርቷንም ጠብቀው ያለፉባት፣ በአሁኑ ጊዜም በየዋሻውና በየገደሉ እርሷን ዋልታ ከለላ አድርገው በጸሎትና  በምናኔ ተጋድሎአቸውን እያካሄዱባት ያሉት፣ አማራጭና መተኪያ የሌላት ቤተ ክርስቲያናችን ከአብራኳ ያልወጡ የፖለቲካ ሰዎችና ብልጣ ብልጦች ቤተ ክርስቲያኗን የፖለቲካ ዓላማቸውና ግላዊ ጥቅማቸው ማሳኪያና ፋይናንስ ማድረጊያ አድርገው ሲጠቀሙባትና የዋሁ ምእመንዋንም ሀገር ወዳድነቱንና በመሀከሉ ያለውን ወቅታዊ ፖለቲካዊ አለመግባባት ተገን በማድረግ፡ እንዲሁም ቀኖናዋንና ዶግማዋን አበክሮ አለማወቁን አውቀው ቤተ ክርስቲያኗን ሲዘርፉ ህዝቡን ሲጫወቱበትና ሲያዋርዱት የሚቆረቆርላቸውና መብታቸን የሚያስከብርላቸው አካል አለመኖሩና አንዳንድ የዋህ ምእመናን

ከእነዚህ ጸረ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችና መሳሪያዎቻቸው ጥቂት3 ካህናት ጎን ሆነው ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜአቸውን በየዋህነት በታቦትና በቤተ ክርስቲያንዋ ስም የፖለቲካዊ ዓላማ ማሳኪያና የግለሰብ ሀብት ማዳበሪያ ማድረጋቸውና ለቤተ ክርስቲያኗና ለምእመናንዋ ጉዳትም እነሱ ራሳቸው መሳሪያ መሆናቸው ነው።

የሆነ ሆኖ ከላይ በገለጽናቸው የቤተ ክርስቲያኗን ህልውናና አንድነት የሚጻረሩና ቀኖናዋንና ሥርዓቷን የሚያፋልሱ ጥፋቶች ላይ በአስተባባሪም ሆነ በተባባሪነት የተሰለፉ ሁሉ ከዚህ ኃላፊነት የጎደለው ሥራቸው እንዲቆጠቡና እግዚአብሔርን፣ ቤተ ክርስቲያኗንና፣ ምእመናኗን እንዲያከብሩ እያሳሰብን፣ ይህን ባያደርጉ ግን የቤተ ክርስቲያኗ ራስ የሆነው ክርስቶስን መሪና አጋዥ በማድረግ ህጓንና ሥርዓቷን ትምህርቷንም እስከ አልጠበቁና በሲኖዶሷ እስከአልተመሩ ድረስ ስሟን እንዳይጠቀሙ ማድረግ የሚቻል መሆኑንና ለቤተ ክርስቲያናችን ህልውናና ክብር ስንል ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር በመተባበር የምንችለውን ሁሉ የምናደርግ መሆናችንን በአጽንኦት እንገልጻለን። ይህን ስንልም ማስፈራሪያ እንዳይመስላቸው ራሳቸው የህግ ባለሙያዎች መጠየቅ የሚችሉ መሆናቸውንና ከአሁን በፊት ተሞክሮ በቀላሉ የተፈጸመ ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ልንገልፅላቸው እንወዳለን።

እንኳን ለ2000 ዓመታት የኖረች፣ በዓለም የታወቀች ብቸኛ ቅድስት ተቀዋም ***“የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን”*** ይቅርና ከዋናው ካምፓኒ እስካላስፈቀዱና በህጉ እስከ አልተመሩ ድረስ ሰበን ኢለበን (7-Eleven) ብሎም መክፈት እንደማይቻልና በድፍረት ከከፈቱም ዝጋ ወይም በህጉ መሠረት ኑር፣ ለስሙም በየወሩ ወይም በየዓመቱ ይህን ያህል ትከፍላለህ ሲባሉ አይሆንም ቢሉ ስሙን መነጠቅ ብቻ ሳይሆን የሚያሳስርም ወንጀል መሆኑን የማያውቅ ያለ አይመስለንም።

ውድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ወገኖቻችን ሆይ! “ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ ዥግራ ናት ይሏታል” እንደሚሉ ቀኖናዋና ዶግማዋን ትምህርቷንም ለመሻርና ህገ ወጥነታቸው ለማስፋፋት እንዲሁም ከላይ እንደገለጽነው ቤተ ክርስቲያኗን የፖለቲካ ምሽጋቸውና ያለ ተቆጣጣሪ  የሀብታቸው ማዳለቢያ የገንዘብ ምንጭ ለማድረግ እንዲያመቻቸው ሲሉ አቡነ መርቆሬዎስ ሪዛይን አላደረጉም አቡነ ጳውሎስ በትክክል አልተመረጡም እያሉና ሌላም ሌላም ሰንካላ ምክንያቶችን እየደረደሩ የበግ ለምድ ለብሰው ሲሸነግሏችሁና ሲያታልሏችሁ ጊዜአዊ የሆነ ፖለቲካዊና መሰል ዓለማዊ ስሜታችሁን መቆጣጠር አቅቷችሁ ለዓመታት የዚህ እኩይ አላማቸው ማሳኪያና የገቢ ምንጫቸው ሆናችሁ ባለማወቅ የእናት ቤተ ክርስቲያናችሁን አንድነት ስትጎዱ ኑራችኋል።

አንድ ጠንቅቃችሁ መረዳትና ማስተዋል ያለባችሁ ይህች ቤተ ክርስቲያን የአባቶቻችሁ የመንግሥተ ሰማያት በር ሆና የኖረችና የእናንተም ሆነ የልጆቻችሁ የልጅ ልጆቻችሁ አማራጭና መተኪያ የሌላት የዘለዓለማዊው ቤታችሁ በር ስለሆነችና ሀብተ ውልድና ስመ ክርስትናን የሰጠቻችሁ ያለ ክፍያና አድልዎ በእውነተኛ ልጆችዋ ካህናት ያስተማረቻችሁና ኮትኩታ ያሳደገቻችሁ እናታችሁ ቀኖናዋን፣ ዶግማዋን፣ ትምህርቷን፣ ዓላማዋንና ህልውናዋን የመጠበቅና የማስጠበቅ የውዴታ ግዴታ እንዳለባችሁ ማወቅና ንስሐ ካልገቡና ቤተ ክርስቲያኗንና ተከታዮችዋን ይቅርታ ካልጠየቁ በየአጥቢያችሁ ያሉትን የእናት ቤተ ክርስቲያናችን ጡት ነካሾች እንዲታረሙ ማድረግ፤ ካልታረሙም መንጥራችሁ ለማስወጣት ህጉ ከጎናችሁ መሆኑን ነው።

## "ዘቦ እዝን ሰሚአ ለይስማእ።" "የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ።" ማር 4፡23

እናንተን የሚያታልሉበትና የሚሸንግሉበት አንደበት ከልጅነታቸው ጀምረው የተካኑትና የምትጠሉትንና የምትወዱትን ጠንቅቀው ያወቁ እንዲሁም ብዙዎቻችሁ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቃችሁ አለማወቃችሁን ከጥንቱ ከጥዋቱ ያጠኑ ስለሆነ የምትወዷቸውን ቅዱሳንን ፈለግ ሳይከተሉ እናንተን ለመሸንገል ስማቸውን ብቻ መቶ ጊዜ ደጋግመው እየጠሩ ባለውለታችሁ የሆነች እናት ቤተ ክርስቲያናችሁን በማትጠቀምበት መንገድ ገንዘባችሁ ስንቱን ቤተ ክርስቲያን ማስገልገና ማሠራት ሲችል የአሜሪካ ባንክ ማጣበቢያ እየሆነ ከመኖሩም አልፎ ለእናት ቤተ ክርስቲያናችሁ ሥርዓት ማፋለሻ እንዲሁም ለህልውናዋ ነቀርሳ መሆኑን መረዳታችሁና መንቃታችሁ ያለፈው ይብቃችሁ፣ በቃን ማለታችሁ የህግ እርምጃ ተወስዶ እንደገና በልመናና በማታለል በሰለጠነ አደበታቸው ገንዘባችሁንና ንብረታችሁን ለአሜሪካ ሀብታም ጠበቆች ከመዋሉ በፊት አማራጭ መድኃኒት መሆኑን መረዳትና ማስተዋል ይኖርባችኋል።

በዚህ አጋጣሚም በዚህ ሀገር ህግ በታክስ ከፋዮች ማለት በህዝብ የሚረዳ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ሌላ ሀይማኖታዊ ተቅዋም (non-profit organization) ውስጥ ደግፎም ሆነ ተቃውሞ ፖለቲካዊ የሆነ ንግግር ከተደረገና ተመሳሳይ ጎሳዊና አድላዊ ሥራም ከተሠራ የሚከስና አስተርጉሞ መረጃ የሚያቀርብ ሲገኝ የቤተ ክርስቲያኑን ወይም የተቅዋሙን ከታክስ ነጻ የመሆን መብቱ የሚያስነጥቅና ድርጊቱን የፈጸሙት ሰዎችንም በህግ የሚያስጠይቅና የሚያስቀጣ መሆኑን ምክራችን ልንለግስላቸው እንወዳለን። መረጃ ካስፈለገም ባለፈው የአሜሪካ ምርጫ በቤተ ክርስቲያን መድረክ አንዱን ሲቃወሙ ሌላውን ሲደግፉ የታዩ ቤተ ክርስቲያናት IRS ከሶ ቁም ስቅላቸው እያሳያቸው እንደሆነ በቅርቡ በዜና አውታሮች የታየ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በአንጻሩም ቀኖናዋና ዶግማዋን ትምህርቷንም ለማስጠበቅና ለማስከበር ደፋ-ቀና የሚሉ ያሉትን ምርጥ ልጆቿ ዋጋን የማያጠፋ የቤተ ክርስቲያኗ መስራችና ራስ የሆነው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ኵሉ እንከ ዘየአምን ብየ በቅድመ ሰብእ አነሂ አአምኖ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት..."፤ "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፣ ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ።" (ማቴ 10፡32-33፤ ማር 8፡38፤ ሉቃ 12፡8) ያለውን ዘለአለማዊ ቃሉን በማስታወስና ይህንን አምላካዊ ቃል መርህ በማድረገ ከላይ የተገለጹት ህገ ወጦችና በጊዜአዊ የፖለቲካም ሆነ ሌላ ጥቅማ ጥቅም ወጥመዳቸው በተጠለፉ ወይም የተታለሉ የተወሰኑ የዋህ የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች ዛቻና አሉባልታ ሳይሰናከሉና ሳያማርሩ ጸንተው አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ ምክራችንን ከአክብሮት ጋር እንለግሳለን።

<u>ማሳሰቢያ፡</u>

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ **ክፍል ሁለት** የተዘጋጀ ሲሆን ይህን ጽሑፍ አይተው ካልታረሙና ማሻሻያ እርምጃ ካልወሰዱ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማዘጋጀት ያነጋገርናቸው ታዋቂ የዩኒቨርስቲ የህግ ፕሮፌሰሮችና፣ ቀላል ኬዝ ነው ማሸነፋችን የማያጠራጥር ስለሆነ ወጭውን የሚሸፍኑ በጎ አድራጊ ድርጅቶችን እንፈልጋለን ካላገኘን የማያስከፍሉ ወይም መጠነኛ ክፍያ የሚጠይቁ ለፍትህና ለርትእ የተቋቋሙ በመንግሥትና በበጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚረዱ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የህግ ተቅዋማት ሊያገኙልን እንደሚችሉ ቃል የገቡልን የተለያዩ የህግ ተቅዋማት ጠበቆች እዲሁም በጥናቱ ያሰባሰብናቸው መረጃዎች ለቅዱስ ሲኖዶስና ቅዱስ ሲኖዶስ ለወከላቸው እውነተኛ ተወካዮች በማቀበልና በመተባበር እየተነጋገርን አስፈላጊ የሆነ የህግ እርምጃ እስኪወሰድ ድረስ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች እውነቱን ታውቁ ዘንድ የምናሰራጨው መሆናችንን ቃል እንገባለን።

<u>የጽሁፉ ይዘትም፤</u>

የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪ ካህናትና በቤተ ክርስቲያኗ ስም የተቋቋሙ ተቅዋማት መሪዎች የቤተ ክርስቲያኗን ቀኖናና ትምህርቷን የማይጠብቁበትና በሲኖዶሷ ሥር የማይኖሩበት ምክንያት ማለት ከፖለቲከኞች ጋር አብረው ቤተ ክርስቲያኗንና ምእመናኗን አቡነ መርቆሬዎስ ሪዛይን አላደረጉም አቡነ ጳውሎስ በትክክል አልተመረጡም እያሉና እንዲሁም የተለያዩ ተልካሻ ዘዴዎች እየተጠቀሙ በአሁኑ ጊዜ የህብረተ ሰባችን ደካማ ጎን የሆነውን የዘር ጥላቻና ፖለቲካ ተገን በማድረግ ቤተ ክርስቲያኗንና ምእመናኗን ሲጎዱ፣ ሲሸነግሉና ሲያታልሉ የሚሩባቸው ወይም የሚታዩባቸው ያሉ ዋና ዋና ምክንያቶች፣

1. ከፖለቲከኞች የሚሰጣቸው የተለያየ ጥቅማ ጥቅም፣ ድጋፍና ገንዘብ እንዳይቀርባቸው፣
2. ጊዜአዊና ዓለማዊ የሆነ የፖለቲካና ጎሳዊ ስሜታቸው ለማርካት ሲሉ፣
3. ጊዜአዊና ዓለማዊ የሆነ የፖለቲካ ስሜታቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው በፖለቲከኞችና በአፈ ጬሌዎች እየተታለሉ በታቦትና በቤተ ክርስቲያኗ ስም ለእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ጥፋት ማለት ለቀኖናዋ፣ ለዶግማዋ፣ ለትምህርቷ፣ ለሥርዓቷም መፋለስ ሳያውቁና ሳይረዱ የፖለቲከኞችና የጥቅም አዳሪ ካህናት የገቢ ምንጭና የሀብታቸው ደላቢ ከሆኑት ከየዋህ የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች ጋር እንዳይጣሉ በማሰብና በመፍራት፣
4. የቤተ ክርስቲያኗንና በቤተ ክርስቲያንዋ ስም የተቋቋሙትን ተቅዋማት ገንዘብ የበላይ ተቆጣጣሪ በሌለበት እንደፈለጉ ለመጠቀምና ለማባከን እንዲያመቻቸው፣
5. አንዳንዶቻቸው ደግሞ ያለ አቅማቸውና ያለ ትምህርታዊ ደረጃቸው የያዙትን ሥልጣን እንዳይነጠቁ በመፍራት ወዘተ... መሆኑን የሚያጋልጥ በደንብ ተጠንቶ የተጻፈ ጥናታዊ ጽሑፍ ነው።

<u>የመጨረሻ ምክር፡</u>

ቤተ ክርስቲያንና የዘር ጥላቻ፣ ፖለቲካ፣ ገንዘብ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። መመሪያችን በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንድሚገኘውና ራሱ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ድርስቶስ እንደተናገረው ለሁለት ጌታ መገዛት አይቻልም። አንዱን ይወዳሉ ሌላውን ይጠላሉ። ስለሚል የእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ሥራ ይሥራ። የፖለቲካ፣ የገንዘብ፣ የዘር ችግር ያለበት ሌላ መድረክ ፈልጎ አላማውን ያካሂድ በሁለት ቢላዋ መብላት ይቅር። ለምድራዊውም ሆነ ሰማያዊ ህይወታችሁ ጥፋት ነውና።
የዘለዓለማዊው ቤታችን በር የሆነች ቤተ ክርስቲያናችን በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በቅዱሳን አባቶቻችን ጸሎት፣ በእውነተኛ ልጆቿ ብርታት ቀኖናዋንና ዶግማዋን ትምህርቷንም ተጠብቆ ለዘለዓለም ይኖራል።

የአባቶቻችን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችንን፣ ሀገራችንንና ህዝባችንን በሰላም፣ በፍቅርና በአንድነት ይጠብቅልን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!     አሜን።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ማህበረ ሰላም የኢትዮጵያውያን ወጣቶች መንፈሳዊ ማህበር
መስከረም 1999 ዓ.ም., Y W

**"ዘቦ እዝነ ሰሚአ ለይስማእ።" "የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ።" ማር 4፥23**

ማህበረ ሰላም የኢትዮጵያውያን ወጣቶች መንፈሳዊ ማህበር ከቤተ ክርስቲያናችን አብራክ ሥር ባደጉና ቅዱስ ዳዊት "እስመ ቅንዓተ ቤትከ በልአኒ"፣ "የቤትህ ቅናት በላኝ" (መዝ 68፡9፤ ዮሐ 2፡17) እንዳለው ስለ እግዚአብሔር ክብር፣ ስለቤተ ክርስቲያኗ አንድነት፣ እድገት፣ ህልውናና፣ ስለ ምእመናንዋ በፍቅር፣ በአንድነት፣ በሰላም መኖርና፣ ስለ ድኅነታቸው፣ የሚቀረቀርና ከላይ ለጠቀስናቸው ቅዱስ ዓላማዎች ተግባራዊነትና ለተተኪ ትውልድ (ወጣቶች) ለማስተላለፍ ሌት ከቀን የሚሠራ መንፈሳዊ ማህበር ነው።

በፈረንጆች አቆጣጠር ከ1999 ጀምሮ በቨርጂኒያ ስቴት ህጋዊ ፈቃድ አግኝቶ በቨርጂኒያ ስቴት የሚገኙ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥና በአካባቢው የሚማሩትንና የሚኖሩትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኝ ወጣቶች፡

- *ሃይማኖታቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ፤*
- *የወንጌልን ዝናር እንዲታጠቁ፤*
- *በመንፈሳዊ ህይወት እንዲልቁ፤*
- *ከአልባሌ ነገሮች እንዲርቁ፤*
- *ለመንግስተ ሰማይ እንዲበቁ፤*

በማስተማርና በማስተባበር ያለ ከላይ እንደተጠቀሰው ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለቤተ ክርስቲያናችን አንድነት፣ እድገትና ህልውና ለምእመናኗም ፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነት፣ ደኅነት፣ ብሩህ የሆነ፣ ግላዊና ጎሳዊ ጥቅም አዘል ያልሆነ ራእይ ያለውና ለተግባራዊነቱም ሌት ከቀን የሚሠራ መንፈሳዊ ማህበር ነው።

የእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኗ ልጅ አስተያየት፣ ተሳትፎና ድጋፍ አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለንና አስተያየታችሁንና ድጋፋችሁን ጻፉልን።

አስተያየት ወይም ሐሳብ፡ email to: mezimur@yahoo.com ወይም
በኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ማህበረ ሰላም የኢትጵያውያን ወጣቶች መንፈሳዊ ማህበር
P.O.Box 1004
Fallschurch, VA 22041 ብለው ይጻፉልን።

*ማባዛት፣ ማሰራጨት፣ ይዘቱን ሳይቀንሱና ሳይጨምሩ መልሶ ማተም፣ በሬዲዮ ማስተላለፍ ይቻላል።*